AMHARIC

# ልዩ ትምህርት እና የአካለ መጠን እድሜ

## “የአካለ መጠን እድሜ” ምንድን ነው?

በኮመንዌልዝ ኦፍ ቨርጂኒያ፣ አንድ ተማሪ <u>በ18ኛ አመት የልደት ቀኑ/ኗ</u> <u>ለአካለ መጠን ይደርሳል/ትደርሳለች</u> እናም፡

- በህግ ፊት እንደአዋቂ ይቆጠራሉ
- በህግ ምርጫ ለመምረጥ ይችላሉ
- ሃላፊነት የሚወስዱባቸውን ኮንትራቶች መፈራረም ይችላሉ

በአብዛኛው ሁኔታዎች፤ አንድ ሰው የአካለ መጠን እድሜ ሲደርስ/ስትደርስ፣ በትምህርት ቤት ስርዓት የተሰጠ የልዩ ትምህርት መብት ወዲያውኑ ከወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ወደ ተማሪው/ዋ ይተላለፋል።

## የአካለ መጠን እድሜ FAQs

(ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች)

**በፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS) የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘሁ ያለሁ ተማሪ ከሆንኩ፣ ለምንድነው “የመብት ማስተላለፍ” አስፈላጊ የሆነው?**

- ከ18ኛ አመት ልደታችሁ ቢያንስ አንድ አመት ቀደም ብሎ፣ FCPS ለአንተ/ለአንች እና ለወላጆቻችሁ ወይም ለአሳዳጊዎቻችሁ ይህ የመብት ሽግግር እንደሚካሄድ ለማሳወቅ በህግ ይገደዳል። በ18ኛ የልደት ቀናችሁ በህግ ፊት እንደ አዋቂ ሰው ትቆጠራላችሁ። ከዚያም እራሳችሁን ለመደገፍ እና የትምህርት መርሃ ግብራችሁን በሚመለከት የራሳችሁን ውሳኔዎች የማድረግ ሀላፊነት አለባችሁ። ምክር ለማግኘት በወላጆችዎ ወይም በአሳዳጊዎችዎ ላይ መተማመንዎን መቀጠል ትችላላችሁ። ስትፈልጉ ወይም ስትጠይቁ ተጨማሪ ምክር እና ድጋፍ ለመስጠት አስተማሪዎቻችሁ እና የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎቻችሁ ይኖራሉ።

**የአካለ መጠን እድሜ ላይ ስደርስ ምን አይነት ለውጦች ይከሰታሉ?**

የአካለ መጠን እድሜ ላይ ስትደርሱ የሚከሰቱ ለውጦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ሁሉም አስፈላጊ ማሳሰቢያዎች ለእናንተ እና ለወላጆቻችሁ ወይም ለአሳዳጊዎቻችሁ መቅረብ አለባቸው
- ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች የተሰጡ ሁሉም መብቶች ወደ እናንተ እንዲተላለፉ እና FCPS ስለ መብቶች መተላለፍ ለሁለቱም ወገኖች ማሳወቅ አለበት
- ስለ ግለሰባዊ የትምህርት መርሃግብራችሁ (IEP) ውሳኔዎች መስጠት ላይ የመሳተፍ መብት አላችሁ
- የእናንተን IEP የመፈረም መብት አላችሁ
- መልካም ትምህርታዊ ምርጫዎችን የማድረግ ኃላፊነት እና ለራሳችሁ ለመቆም እና ቀዳሚ ሚና አለባችሁ

**IEP ለእኔ ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?**

**<u>የእናንተ</u>** IEP ነው።  እንደ አካል ጉዳተኛ ተማሪ እናንተ ልታገኟቸው የምትችሏቸውን አገልግሎቶች የሚገልጽ ህጋዊ ሰነድ ነው። EP አሁን ያለዎትን የትምህርት አፈጻጸም ደረጃ ይገልፃል፣ ግላዊ ግቦችን እና አላማዎችን ያጠቃልላል፣ በክፍለ ሃገር እና በFCPS ግምገማዎች ላይ ስላሎት ተሳትፎ መረጃ ይሰጣል እና ስለትምህርት ፕሮግራምዎ ሌሎች መረጃዎችን ይገልጻል። IEP በወላጆችዎ፣ በአስተማሪዎቻችሁ፣ በሌሎች የትምህርት ቤት ባለሙያዎች እና በአንተ/በአንች በተማሪው/ዋ መካከል ግንኙነትን ለማረጋገጥ የተነደፈ ሰነድ ነው።

**ለአካለ መጠን እድሜ ስደርስም IEP የሚያስፈልገኝ ለምንድን ነው?**

የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) በሕዝብ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎች IEP እንዲኖራቸው ያስገድዳል። ይህ ሰነድ የተጻፈው በተለይ የእናንተን የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት ነው።

**በ IEP ቡድን ስብሰባዬ ውስጥ ስሳተፍ ወይም ስለ እኔ IEP ውሳኔ ሳደርግ፣ ስለ እኔ ምን አይነት ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው?**

እናንተ እና የብድኑ አባል ከዚህ በታች ያሉትን ማሰብ አለባችሁ፡

- ጥንካሬዎች
- ፍላጎቶች
- መሻሻል የሚፈልጉ ክፍሎች
- መሻሻል የሚፈልጉ ክፍሎችን የማሻሻያ መንገዶች
- የትምህርት መማሪያ ዘዴዎች እና ምርጫዎች (እንዴት በፍጥነት ይማራሉ)
- በአጠቃላይ ትምህርት እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎ
- ለምደባ እና ለፈተናዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የቀለም ትምህርት እና የሞያ መስክ ግብ
- የድህረ-ምረቃ እቅዶች

**በ IEP ቡድን ስብሰባ ወቅት የእኔ ሚና ምንድን ነው?**

በ IEP ቡድን ስብሰባ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ሆናችሁ ማገልገላችሁ አስፈላጊ ነው። የትምህርት መርሃግብራችሁን በሚመለከት በመረጃ ላይ የተመረኮዙ ውሳኔዎችን በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ትጫወታላችሁ። የሚከተሉትን ካደረጋችሁ ይህ ሊሳካ ይችላል።

- የቡድኑ አባላት የእናንተን የግል ግቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ
- የእናንተን ጥንካሬ እና ድክመቶች ግምት ውስጥ አስገቡ
- ለወደፊት የመማር ልምዶች እቅዳችሁን ተወያዩ
- ግባችሁን ለማሳካት ስትሞክሩ ጠቃሚ ሆነው ያገኛችኋቸውን ልዩ ስልቶች ለዩ
- የሙያ ፍላጎታችሁን በግልጽ ግለጹ፤ እንዲሁም እንዴት እነሱን ማሳካት እንደምትችሉ ተወያዩ
- አስተማሪዎቻችሁ እና አስተዳዳሪዎቻችሁ እናንተን መርዳት እንደሚቀጥሉ አስታውሱ

## ዝግጁ ናችሁ?

የጉርምስና ዕድሜን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ እባካችሁ የፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ፍትሃዊ ሂደት እና ብቁነት (FCPS) በስልክ 571-423-4470 ወይም በፋክስ በ571-423-4037 ያግኙ።

ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ለልጃቸው ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ማድረጋቸውን መቀጠል አስፈላጊነት ካሳሰባቸው፤ *ለአዋቂ ተማሪዎች የትምህርት ውክልና የሚለውን መፅሄት ይመልከቱ።*

## ለጥያቄዎች ወይም ተጨማሪ መገልገያ አቅርቦቶች

**የትምህርት ቤትዎ የስራ ቅጥር እና ሽግግር ተወካይ (ETR)**

**የትምህርት ቤትዎ የልዩ ትምህርት ክፍል ሃላፊ**

**የሞያ መስክ እና ሽግግር አገልግሎት**
571- 423- 4150

**በፍትህ መዳኘት እና ብቁነት**
571- 423- 4470

**ከላይ ያሉትን መስሪያ ቤቶች ጋር በእነዚህ አድራሻዎች መገናኘት ይቻላል፡**
8270 Willow Oaks Corporate Drive
Fairfax, Virginia 22031

**ፌርፋክስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች**
ዶክተር ሚሽል ሪድ፣ ሱፐርኢንተንደንት
8115 Gallows Road
Falls Church, Virginia 22042
571-423-1200

